የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ በሚነሶታ የህንፃ መስራች ግብረ-ኃይል
ECMbuildingtaskforce@yahoo.com

**በሚኒያፖለስ፣ በሴንትፖልና በአከባቢው ለምትኖሩ የህንፃ ግዢ ድጋፍ ሰጭ ኢትዮጵያውያን በሙሉ**

በቅድሚያ የከበረ ሰላምታችን እያቀረብን የኮሙኒታችንን ህንፃ ለመግዛት እስከአሁን ላደረጉት ወይም ወደፊት ለሚያደርጉት የገንዘብ መዋጮና ድጋፍ ምስጋናችን ከፍ ያለ ነው።

የህንፃ መስራች ግብረኃይል በአካባቢያችን ያሉ ኢትዮጵያውያንን አሰባስበንና አስተባብረን ገንዝብ በማሰባሰብ ለሃዘናችንም ሆነ ለደስታችን መሰባሰቢያና መገናኛ እንዲሁም ለበዓላችን ማክበሪያ አንድ ማዕከል ለመግዛት ከመቼውም የበለጠ ጠንክረን በመስራት ላይ እንገኛለን።

ስራችን ከጀመርንበት ከMay 18, 2013 ጀምሮ እስከአሁን ድረስ ባደረግነው ጥረት አርባ ስምንት ሺህ የአሜሪካ ዶላር ያሰባሰብን ሲሆን አሁን ደግሞ አምስት ሺህ ቲኬቶችን በማስተም አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ዶላር በመሸጥ ያቀድነውን ህንፃ ለመግዛት ዕቅድ አውጥተን የግብረ-ኃይላችንን አባላት በቤተክርስቲናት፣ በመስጊዶችና በተለያዩ የኢትዮጵያውያን ድርጅቶች አሰራጭተን ትኬቶችን በመሸጥ ላይ ስንሆን በሌላ በኩል ደግሞ አትራፊ ካልሆኑ የውጭ ድርጅቶች ዕርዳታ የምናገኝበትን መንገድ አጥንተን የተለያዩ የድርጅት ተወካዮችን በማነጋገር ላይ እንገኛለን

በዕቅዳችን መሰረት ህንፃውን ከገዛን በኃላ የምናስረክበው በህዝብ ለተመረጡ የአመራር አባላት ሲሆን ለዚህ ህንፃ ገንዘብ ያዋጣው ህዝብ ሁሉ ስለ ህንፃው ሊወያይም ሆነ ሊወስን ይገበዋል ብለን እናምናለን። አሁን በአመራር ላይ ያሉትና አገልግሎታቸውን የጨረሱት የአመራር አባላት ግን ህዝቡን በማሳተፍ አስመራጭ ክሚቴ አስመርጠው እንዳለፉት ሃያ ዓመታት ምርጫውን ግልፅና ፍትሃዊ ማድረግ ሲገባቸው እራሳቸው አስመራጭ ኮሚቴ በመሰየም ህዝብ የማያውቀውና አምበገነናዊ ቦርድ የሚመራው የጠቅላላ ጉባዔውን ድምፅና ሙብት የሚገድብ መተዳደሪያ ደንብ በማምጣት ኮሚኒቲውን አባላት ሊወስኑና ሊቆጣጠሩት ወደማይችሉት አቅጣጫ በመምራት ላይ ይገኛሉ። አስመራጭ ኮሜቴ መምረጥ የጠቅላላው ጉባኤው ሙብትና ኃላፊነት ሲሆን አሁን ባመጡት መተዳደሪያ ደንብ ግን አስመራጭ ኮሚቴ የሚመርጡት እራሳቸው ጊዜያቸውን የጨረሱት የአመራር አካላት ናቸው። ይህን ፀረ ዲሞክራሲያዊና የህዝብን ሙብት የሚጋፋ አሰራር እኛ የህንፃ መስራች ግብረኃይል ተወያይተን በአንድ ድምፅ የተቃወምንና ያወገዝን ሲሆን ይህን አምባገነናዊ እንቅስቃሴ የተቃወሙ ሌሎች ኢትዮጵያውያንም የፊርማ ማሰባሰብ እንቅስቃሴ በማድርግ ላይ ናቸው።

ዲሞክራሲና ግልፅነት ያለው የምርጫ ስርዓት ተካሂዶ የህንፃ ግብረ ኃይሉ በሕዝብ ከሚመረጠው አዲስ የኮሚኒቲ አመራር ጋር የጀመረውን ሥራ በአግባቡ መቀጠል ይችል ዘንድ አባል በመሆን ከሚያዝያ 30, 2015 በፊት በኢትዮጵውያኖች በሚደረገው የፊርማ ማሰባሰብ ላይ በመሳተፍ እና እንዲሁም May 16, 2015 ምርጫው ላይ በመገኘት አስመራጭ ኮሚቴው በሕዝብ ተመርጦ መሪዎቻችንን መምረጥ እንድንችል ለግልፅና ፍትሐዊ ምርጫ ለሚደረገው እንቅስቃሴ የበኩሎዎን አስታዋፅኦ እንዲያደርጉ ጥሪያችንን እያቀረብን የአባልነት ግዴታዎን አሟልተው ከሆነ በዚህ ኢሜል አድራሻ በአስቸኳይ እንዲያሳውቁን በጥብቅ እናሳስባለን።

**የህንፃ መስራች ግብረ-ኃይል**

1. ታደሰ ንጋቱ

2. ዘነበች ደምሴ

3. አበባው ይልማ

4. ግርማ ብሩ

5. ማይከ ወርቁ

6. ፈትለወርቅ ተሰማ

7. ዳንኤል ጎበዜ

8. ሙሉጌታ ፈለቀ

የምርጫ ቀን May 16, 2015 ሰዓት 2 pm – 4 pm

አድራሻ 265 Oneida St, St. Paul, MN 55102

ጥያቄ ካለዎት የህንፃን ኮሜቴ ለማግኘት ECMbuildingtaskforce@yahoo.com